፬/ አዋጁን፣ አዋጁን ተከትለው የሚወጡ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን፣ አሰራሮችንና የአጠቃቀም ሥርዓቶችን ማስፈጸም፤ በሚያስፈጽሙ አካላት ላይ የግንዛቤ ማጎልበቻ፣ የእገዛ፣ የክትትል፤ የግምገማ ሥራዎችን ያከናውናል፤ ክፍተቶች ሲገኙም አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፤ ዝርዝር እርምጃዎችን በሚመለከት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ተግባራዊ ማድረግ፤

4/ enforce the Proclamation, Regulations and Directives, practices, working procedures issued and in place in accordance with the Proclamation; aware, follow up and assist those organs enforcing them, report and recommend to the Ministry on the necessary administrative measures to remedy the gaps; execute measures to be enacted through Directives to be issued by the Ministry;

፭/ ከመንገድ ትራፊክ ደህንነት አንጻር የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት ወይም ማንኛውም ተሽከርካሪ ሊያሟላው የሚገባውን የደህንነት መስፈርት በየጊዜው እያጠና ለሚመለከተው አካል ማሳወቅና አፈጻጸሙን መከታተል፤

5/ undertake studies and forward its findings relating to road traffic safety to concerned organs regarding requirements to get driving permit and requirements of any vehicle to be set as road worthy; and follow up its implementation;

፮/ በሚመለከታቸው አካላት የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚከናወኑ ተግባራት የተቀናጁና ከሀገራዊ የአጭር፤ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ግቦች ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ ማስተባበር፤

6/ ensure and coordinate road traffic safety and traffic management activities undertaken by concerned organs are integrated and consistent with the national short; medium and long term road traffic safety goals;

፯/ በሚመለከታቸው አካላት ለሚተገበሩ ሀገር አቀፍ የመንገድ ደህንነትና የትራፊክ ማኔጅመንት እቅዶች ማስፈፀሚያ የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ ማድረግ፤

7/ extend technical and financial assistance for the execution of national road safety and traffic management plans undertaken by concerned organs;

፰/ ሀገራዊ የመንገድ ደህንነትና የመንገድ ትራፊክ ማኔጅመንት እቅድ አፈፃፀሞችን መከታተልና መመዘን፤ ሀገር አቀፍ የአፈፃፀም መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማደራጀትና ለሚመለከታቸው አካል ማሰራጨት፤

8/ assess and evaluate the national road safety and traffic management performances; organize national performance data and disseminate them to concerned organs;

